# 12ኛ ትምህርት

*ከታህሣሥ 1-7 2009 ዓ.ም* *Dec 10—Dec 16*

# የኢዮብ ቤዛ

ሰንበት ከሰዓት

ለዚህ ሣምንት ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ኢዮ. 19:25-27፣ ዮሐንስ 1:1-14፣ ኢዮብ 10:4 እና 5፤ ሉቃስ 2:11፤ ገላ. 4:19፣ ሉቃስ 9:22፣ ኢሳ. 53:1-6።

> ***መታሰቢያ ጥቅስ፡-*** **‹‹በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ ሕመማችንንም ተሸክሞአል፤ እኛ ግን እንደ ተመታ በእግዚአብሔርም እንደ ተቀሠፈ እንደ ተቸገረም ቈጠርነው።›› (ኢሳ. 53:4)**

ጌ ታ ራሱ በድንገት ሲገለጥ ከምዕራፍ 38 ጀምሮ የኢዮብ መጽሀፍ ወደ ታሪኩ ጡዘት ይደርሳል። እግዚአብሔር ራሱን ለኢዮብ በኃይለኛ እና ተዓምራዊ መንገድ ገለጠለት፤ ይህም ኢዮብ ወደ ንስሐ እና ኑዛዜ እንዲገባ አደረገው። ከዚያም የኢዮብን ሶስት ወዳጆች ስለ ተናገሩት የተሳሳቱ ቃላት ጌታ ገሰፃቸው፤ እንዲሁም ኢዮብ ደግሞ ስለ እነሱ ፀለየ። ‹‹ኢዮብም ስለ ወዳጆቹ በጸለየ ጊዜ እግዚአብሔርም ምርኮውን መለሰለት፤ እግዚአብሔርም ቀድሞ በነበረው ፋንታ ሁለት እጥፍ አድርጎ ለኢዮብ ሰጠው።›› (ኢዮብ 42፡ 10) እናም ረጅም እና ሙሉ የሆነን ሕይወት ከዚያ በኋላ ለመኖር በቃ።

ነገር ግን ስንመለከተው ታሪኩ በሚያበቃበት ሁኔታ ላይ አንድ የሚጎረብጥ እና የማያረካ ነገር አለ። እግዚአብሔር እና ሰይጣን በሰማይ ክርክር ገጥመው ሲያበቁ በምስኪኑ ኢዮብ ህይወት እና ስጋ ላይ ጦርነት መግጠማቸው ልክ ነው? ፍጹም ፍትሀዊም ትክክልም አይመስልም፤ ያውም ጌታ በሰማይ ሆኖ ይህንን እየተመለከተ በእግዚአብሔር እና በሰይጣን መካከል ባለው በዚህ ግጭት ምክንያት ኢዮብ የስቃይን ገፈት መቅመሱ ትርጉም አይሰጥም።

ከታሪኩ የሚቀረው ነገር ያለ ይመስላል፤ በእርግጥም ደግሞ አለ። ይህ የታወቀው ከብዙ ምዕተ ዓመታት በኋላ በኢየሱስ እና እርሱ በመስቀል ላይ በመሞቱ ነበር። የኢዮብ መጽሐፍ በሙላት ያልመለሰውን ጥያቄያችንን የምንመልሰውና የሚያሳርፈንን አስደናቂ ነገር የምናገኘው በኢየሱስ ብቻ ነው።

*የዚህን ሣምንት ትምህርት አጥንተው ለታህሣሥ 8 ሰንበት ይዘጋጁ።

*እሁድ ታህሣሥ 2* *Dec 11*

## ቤዛዬ ህያው ነው

በምዕራፍ 38 ላይ እግዚአብሔር ለኢዮብ ሲገለጥ ራሱን ለኢዮብ እንደ ፈጣሪ ነበር ያስተዋወቀው፤ በስራውም ‹‹ ባድማውንና ውድማውን እንዲያጠግብ፥ ሣሩንም እንዲያበቅል፣ ማንም በሌለባት ምድር ላይ፥ ሰውም በሌለባት ምድረ በዳ ላይ ዝናብን ያዘንብ ዘንድ፣ ለፈሳሹ ውኃ መንዶልዶያውን፥ ወይስ ለሚያንጐደጕድ መብረቅ መንገድን ያበጀ፤›› ተብሏል። (ኢዮብ 38፡25-26) የእኛ ጌታ ግን ፈጣሪ ብቻ አይደለም። ሌላ ወሳኝ የሆነ ማዕረግ እና ሚና ጭምር አለው። ኢዮብ 19፡25-27ን ያንብቡ፡ እነዚህ ቃላት ስለ ኢዮብ የድነት ተስፋ ምን ይነግሩናል?

---

በእነዚህ ታዋቂ ጥቅሶች ውስጥ ኢዮብ ስለ ቤዛው ያለውን መረዳት ያሳየናል፤ ምንም እንኳን ሰዎች በሞት ቢለዩንም ከመቃብር በላይ የሆነ ተስፋ አለን፤ ይህ ተስፋ ደግሞ አንድ ቀን ወደ ምድር በሚመጠው ቤዛችን የሚገኝ ነበር።

የኢዮብ ቃላት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በጣም አስፈላጊ እና ጠቃሚ የሆነውን እውነት ያመላክቱናል፡- እግዚአብሔር ቤዛችን ስለመሆኑ። አዎን እግዚአብሔር ነው ፈጣሪያችን፤ ዳሩ ግን በወደቀው ዓለም በኃጢያታቸው ምክንያት ለዘለዓለም ሞት በተዳረጉ ኃጢያተኞች ዓለም ውስጥ ከፈጣሪ የበለጠ ያስፈልገናል፤ የሚቤዠን ጭምር ያሻናል። እናም አምላካችን በትክክልም ፈጣሪያችንና ነው (ኢሳ. 48፡13-17 ይመልከቱ)

ደግሞም እኛ የታላቁን የዘለዓለም ህይወት ተስፋ ያገኘነው ከእነዚህ ሁለት የእርሱ ሚናዎች የተነሳ ነው፡፡

**ዮሐ. 1፡1-14 ን ያንብቡ፡ በዚህ ምንባብ ውስጥ ፈጣሪውን ኢየሱስ እና የሚቤዠንን ኢየሱስ እንዴት ነው ዮሐንስ ያጣመረው?**

---

---

የዘፍ. 1፡1 ማጣቀሻ በድጋሚ በዮሐ1፡1 ላይ ስለ እግዚአብሔር ፈጣሪነት በድጋሚ በግልጽ ተቀምጧል፡፡ እናም ይህ አልበቃ ቢለን በኢየሱስ ፈጣሪነት እና ቤዛነት መካከል የሚገኘው ግንኙነት እንደማይነጣጠል በእነዚህ ቃላት ተረጋግጦ እናገኛለን፡፡ ‹‹በዓለም ነበረ፥ ዓለሙም በእርሱ ሆነ፣ ዓለሙም አላወቀውም፡፡

የእርሱ ወደ ሆነው መጣ፥ የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም፡፡ ለተቀበሉት ሁሉ ግን፣ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፤›› (ዮሐ. 1፡10-12) በእርግጥም ሊቤዠን የቻለበት ምክንያት ፈጣሪያችን ስለነበር ጭምር ነው፡፡

**ቤዛ ሳይሆን ፈጣሪያችን ብቻ የሆነ አምላክ ቢኖረን ኖሮ ምን ተስፋ ይኖረን ነበር? ከመልስዎ በመነሳት ኢየሱስን እንደ ቤዛችን ማየት አስፈላጊ ስለ መሆኑ ምን እንማራለን?**

*ለኞ ታህሣሥ 3* *Dec 12*

## የሰው ልጅ

በኢዮብ መጽሐፍ የመጀመሪያዎቹ ምዕራፎች ውስጥ በክርስቶስ እና በሰይጣን መካከል ስላለው ፍልሚያ

እውነታ በጨረፍታ እንመለከታለን፡፡ እንደምናውቀው ይህ ፍልሚያ የተጀመረው በሰማይ ነበር፤ ዳሩ ግን በሂደት ወደ ምድር መጥቷል (ራዕይ 12፡7-12 ይመልከቱ)፡፡ በኢዮብ መጽሐፍ ውስጥ ይህንኑ እንቅስቃሴ ነው የምናየው፡- ፍልሚያው በሰማይ ተጀምሮ ወደ ምድር ሲመጣ፡፡ አለመታደል ሆኖ በምድር ላይ የነበረው ፍልሚያ በኢዮብ ላይ አተኩሮበት ነበር፡፡

**ኢዮብ 10፡4 እና 5ን ያንብቡ፤ የኢዮብ የቅሬታ ጥያቄ ምን ነበር? ደግሞስ ቅሬታው እውነት አልነበረውም?**

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

**የኢዮብ ሀሳብ ቀላል ነበር፤ አንተ አምላክ ነህ የዩኒቨርስ ልዑል ነህ፣ ፈጣሪ ነህ፤ ሰው መሆን እንዴት ይገባሀል? እኛ የምናየው መከራ በትክክል እንዴት ይገባሀል?**

**የኢዮብን ቅሬታ የሚከተሉት ጥቅሶች እንዴት ይመልሱለታል? ሉቃስ 2፡11፣ ዮሐ.1፡14፣ ሉቃስ 19፡10፣ ማቴ. 4፡2፣ 1ኛ ጢሞ.2፡5፣ ዕብ. 4፡15**

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

ኢዮብ "እግዚአብሔር ሰው ስላልሆነ የሰውን ዋይታ ሊረዳ አይችልም" ያለበት ቅሬታው ሙሉ በሙሉ ኢየሱስ ሰው ሆኖ ሲገለጥ ተመልሶለታል፡፡ መለኮታዊነቱን ባያጣም እንኳን ኢየሱስ ፍፁም ሰውም ነበር፤ እናም በዚህ ስብእናው የስቃይ እና መከራን ምንነት ልክ ኢዮብ እና የሰው ዘር ሁሉ እንደሚጋፈጡት ያውቀዋል፡፡

በእርግጥ በወንጌላት ሁሉ ውስጥ የክርስቶስን ሰው የመሆን እውነታ እና በእኛ ሰብዓዊነት ውስጥ ሆኖ ያየውን መከራ ጭምር እናያለን፡፡ ኢየሱስ የኢዮብን ጥያቄ/ ቅሬታ መልሶለታል፡፡

‹‹ክርስቶስ የተላበሰው ሰብዓዊነት የታይታ ሰውነትን አይደለም፤ ሰብዓዊ ማንነትን ወስዶ በሰብዓዊነት ኖረ፡ ፡ . . . ስጋ መልበስ ብቻ ሳይሆን ኃጢያት በተላበሰው ስጋ አምሳል ነበር የተፈጠረው፡፡›› ኤለን ጂ. ኋይት ማስታወሻ፤ የኤስ.ዲ.ኤ ባይብል ኮሜንተሪ፤ ቅጽ፡ 5፣ገጽ 1124

**ኢየሱስ ሰብዓዊነትን ለበሰ ሲባል ምን ማለት እንደሆነ እስቲ ያስቡ፤ በየትኛውም አሁን በሚገጥምዎት**

**መከራ ውስጥ እርሱ ምን ያህል የውስጥን ሊረዳ እንደሚችል ይህ ምን ያስረዳናል?**

*ማክሰኞ ታህሣሥ 4* *Dec 13*

## የመሲሁ ሞት

**የሚከተሉት ጥቅሶች ስለ ኢየሱስ እና እንዴት ልንመለከተው እንደሚገባ ምን ይነግሩናል?**

1ኛ ዮሐ. 2፡6

---

ገላ. 4፡19

---

ያለ ጥርጥር ኢየሱስ ዋቢያችን ነው። ሕይወቱ እና ባህርይው እርሱን የሚከተሉ ሁሉ ሊሹት የሚገባቸው እና በእግዚአብሔር ፀጋ መምሰል ያለባቸው ነው።እግዚአብሔር የጠራን ዓይነት ሕይወት ለመኖር ምሳሌ ሊሆንልን የሚችለው ብቸኛው ፍፁም ምሳሌ ኢየሱስ ነው።

ቢሆንም ኢየሱስ ወደዚህ ምድር የመጣው ምሳሌ ሊሰጠን ብቻ አይደለም። ኃጢያተኞች ሆነን መገኘታችን ከባህርይ ለውጥ በላይ የላቀ ነገር ያስፈልገው ነበር። ባህሪያችንን ማደስ እና እኛን ወደርሱ ምስል መቀየር የቤዛነት መጠይቁን አይመልስም ነበር። ከዚህ ያለፈ ነገር ያስፈልገን ነበር፣ ምትክ ያስፈልገን ነበር፣ የኃጢያታችንን ቅጣት የሚከፍል ሌላ ያስፈልገን ነበር። ለእኛ ለሁላችንም ምሳሌ የሚሆን ፍፁም ህይወት ለመኖር ብቻ አይደለም የመጣው፤ ለእኛ የሚገባውን ሞት ሞቶ የእርሱ ፍፁም ህይወት የእኛም ሆኖ እንዲቆጠር ጭምር ነው የመጣው።

**የክርስቶስ መሞት ለእኛ አስፈላጊ ስለ መሆኑ የሚከተሉት ጥቅሶች ምን ያስተምሩናል? ማር. 8፡31፣**

**ሉቃስ 9፡22፣ ሉቃስ 24፡7፣ ገላ. 2፡21**

---

---

ኢየሱስ ለህጉ በመታዘዝ ስለ እኛ ሞተልን፤ ህጉ ለክርስትና ማዕከላዊ ቢሆንም የወደቁትን ሊያድን አይችልም፡፡ ‹‹እንግዲህ ሕግ የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል የሚቃወም ነውን? አይደለም፡፡ ሕያው ሊያደርግ የሚቻለው ሕግ ተሰጥቶ ቢሆንስ በእውነት ጽድቅ ከሕግ በሆነ ነበር፤›› (ገላ. 3፡21) የትኛውም ህግ ኃጢትን ሊያድን የሚችል ቢሆን ኖሮ ከሁሉ ይልቅ የእግዚአብሔር ህግ ይቀድም ነበር፡፡ ዳሩ ግን ይህም ህግ ቢሆን ሊያድን አይችልም፡፡ የፍፁም ምሳሌያችን ኢየሱስ ፍፁም የሆነው ህይወት ብቻ ነው የሚያድነን፤ እናም ክርስቶስ ራሱን ‹‹አንድ መስዋዕት ለዘለዓለም›› (ዕብ. 10፡12) በማድረግ ለማቅረብ መጣ፡፡

**የእርስዎ የሕግ አጠባበቅ ታሪክ ምትክ የሚያስፈልግዎ ስለ መሆኑ ምን ያሳይዎታል?**

*ረቡዕ ታህሣሥ 5* *Dec 14*

## የሰው ልጅ መከራ

**ኢሳ. 53፡1-6 ያንብቡ፤ ጌታ በመስቀል ላይ ስላየው ስቃይ ይህ ክፍል ምን ይነግረናል?**

---

ኢሳ 53፡4 ሲናገር ኢየሱስ ደዌያችንን እና ህመማችንን ተሸከመ ይላል፡፡ ይህ የኢዮብን ህመምና ደዌ ጭምር የሚያካትት መሆን አለበት፡፡ እንደውም የኢዮብን ብቻ ሳይሆን የምድርን በሙሉ ነው፡፡ ኢየሱስ በመስቀል ላይ የሞተው በሕይወት ለኖሩ ሰዎች ሁሉ ኃጢያት ሲል ነው፡፡

እንግዲህ የኢዮብ መጽሐፍ በትክክል ሊታይ የሚችለው ከመስቀሉ አንፃር ብቻ ነው፡፡ እዚህ ላይ እግዚአብሔር ራሱን ለኢዮብ ለንስር መብረር የሚያስተምር አምላክ ኢዮብ በራሱ ወይም የትኛውም የሰው

ዘር ሊሸከመው የማይችለውን የስቃይ ሲቃ የሚረዳ አምላክ ሆኖ ነው የተገለጠው፡፡ በየግላችን እኛ የሚገጥመንን ህመም እና ሀዘን አብሮን እርሱም ይሰማዋል፡፡ ማንም ቢሆን እንግዲህ ለእግዚአብሔር ስለስቃይ ሊያስተምረው አይችልም፤ ያውም በሰብዓዊነቱ በዓለም ሁሉ ዙሪያ የተንሰራፋውን የኃጢያት መከራ ገፈት የተጋፈጠው እርሱ ሆኖ እኛ መረዳት የምንችለው የራሳችንን ስቃይ ብቻ ነው፤ የራሳችንን ሀዘን ብቻ፤ በመስቀል ላይ ግን ኢየሱስ የሁሉን ተሸክሟል፡፡

ኢዮብን ‹‹የሰማይን ሥርዓት ታውቃለህን? በምድርስ ላይ እንዲሠለጥን ልታደርግ ትችላለህን?›› ኢዮብ 38፡33) በማለት የጠየቀው እግዚአብሔር ምንም እንኳን ‹‹የሰማይን ስርዓት›› የፈጠረ ቢሆንም ምድራዊ ስጋ በመልበስ በስጋም ሞትን መቅመሱ እና ‹‹. . . ደግሞ በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን በሞት እንዲሽር፣ ይኸውም ዲያብሎስን . . . ›› (ዕብ. 2፡14) እጅግ የሚደንቅ ነው፡፡

ከመስቀሉ አንጻር ሲታይ የኢዮብ መጽሐፍ ለብቻው ከሚታይ ይልቅ የበለጠ ትርጉም ይሰጣል፤ ምክንያቱም መጽሀፉ በእንጥልጥል የሚተዋቸውን ብዙ ጥያቄዎች መስቀሉ ይመልሳልና ነው፡፡ ደግሞም ከጥያቄዎች ሁሉ ትልቁ ኢዮብ በምድር ሆኖ እንደዚያ ሲሰቃይ እግዚአብሔር ደግሞ ይህን ሁሉ የሰይጣን ክስ ለማሸነፍ መሆኑ ምን ያህል ፍትሀዊ ነው የሚል ነው፡፡ መስቀሉ ኢዮብም ሆነ የትኛውም የሰው ዘር በዚህ ዓለም ስቃይ ቢገጥመው ማናችንም ልንቋቋመው ከምንችለው የሚልቅ እጅግ ጥልቅ የሆነውን ስቃይ በፍቃደኝነት መሰቃየቱን ያሳየናል፤ ይህም የደህንነትተስፋ እና ቃል ኪዳን ሊያስችለን በማሰብ የሆነ ነው፡፡

ኢዮብ እግዚአብሔርን እንደ ፈጣሪ አየው፣ ከመስቀሉ በኋላ እኛ ደግሞ እንደ ፈጣሪ እና ቤዛ እንቆጥረዋለን፣ ወይም ደግሞ በተለየ መንገድ ቤዛ የሆነልን ፈጣሪ ሆኗል (ፊሊ. 26፡8) ይህንን ለማድረግም ኢዮብን ጨምሮ የትኛውም የሰው ዘር ሊሸከመው ከሚችለው/ ከሚፈቅደው በላይ መከራን መቀበል ነበረበት፡፡ ስለዚህም እንደ ኢዮብ እኛም ‹‹ስለዚህ ራሴን እንቃለሁ፤ በአፈርና በአመድ ላይ ተቀምጬ እጸጸታለሁ፡፡›› (ኢዮብ 42፡6) ከማለት በስተቀር ይህን አይተን ምን ማለት እንችላለን፡፡

## ሰይጣን ተጋለጠ

ዮሐ. 12፡30-32ን ያንብቡ፤ በመስቀሉ እና በታላቁ ተጋድሎ አንጻር ኢየሱስ ስለ ሰይጣን ምን እያለን ነው?

---

ኢየሱስ በመስቀል ላይ ስለ መሞቱ ከተናገረች በኋላ አሌን ጂ. ኋይት ይህ ክስተት በሰማይ ስለ ነበረው ተጽዕኖ እና በትዝብት ስለ ሚመለከተው ዩኒቨርስ አስተያየት የሚከተለውን ጽፋለች፡፡ ‹‹ በመለኮት ባህርይና በእግዚአብሔር መንግስት ላይ የሚያነሳቸው የሐሰት ክሶች ትክክለኛ መልካቸው ታየ፡፡ “እግዚአብሔር፣ ፍጥረታት በሙሉ እንዲገዙለትና እንዲታዘዙለት የሚፈልገው ራሱን ከፍ ከፍ ለማድረግ ሲል ብቻ ነው” በማለት ክሱን አቀረበ፡፡ “ሌሎች ራሳቸውን እንዲያዋርዱ የሚጠይቀው ፈጣሪ፣ እርሱ ራስን ማዋረድና መስዋዕትነትን መክፈል አይታይበትም” በማለት ቅሬታውን ገልጾ ነበር፡፡ አሁን ግን የዓለማት ገዢ በኃጢዓት ለወደቀው የሰው ዘር ድነት ሲል ከፍቅር የመነጨ ታላቅ መስዋዕትነትን እንደ ከፈለ አየ፡፡ ‹‹እግዚእበሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና›› (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡19)፡፡

ሉሲፈር ለራሱ ክብርንና ታላቅነትን በመመኘት ኃጢዓት ወደ ዓለም እንዲገባ በሩን ሲከፍት ክርስቶስ ደግሞ ኃጢዓትን ለማስወገድ እራሱን አዋርዶ እስከሞት ድረስ የታዘዘ ሆነ፡፡›› (ዘግሬት ኮንትሮቨርሲ ገፅ 502/ ታላቁ ተስፋ ገፅ 15)

**2ኛ ቆሮ.5፡19ን ያንብቡ፤ እንዴት ነው የክርስቶስ ኛ መሞት የወደቀውን ዓለም ከእግዚአብሔር ጋር ያስታረቀው?**

---

---

ዓለም በኃጢያት ወድቋል፤ ዓመፀኛ ሆኗል፤ ለሰይጣን ወጥመዶች የተመቸ ስፍራ ሆኗል፤ ይህም በግልፅ ለምሳሌ በኢዮብ መጽሐፍ ውስጥ ሊታይ ይችላል፡፡ ኢየሱስ ግን ሰብዓዊነትን በመላበስ መለኮታዊነቱን አይተው በሰማይ እና በምድር መካከል የማይበጠስ ትስስርን በሞቱ በማጥበቅ የኃጢያት እና የሰይጣንን

የመጨረሻ ውድቀት አረጋግጧል፡፡ በመስቀሉ ኢየሱስ የኃጢያትን የህግ ቅጣት ከፈለ፤ በዚህም የወደቀውን ዓለም ከእግዚአብሔር ጋር አስታረቀ፡፡ ምንም ኃጢያተኞች እና ሞት የተፈረደብን ብንሆንም በኢየሱስ አማካይነት በእምነት የዘለዓለም ሕይወት ባለ ተስፋዎች ነን፡፡

**የሰሩት ኃጢዓት ምንም ያህል ቢከፋ፣ ለሁሉም ኢየሱስ ሙሉ ዋጋውን ከፍሎልዎታል፡፡ ይህ አስደናቂ የሆነ እውነት የእርስዎን ህይወት በመለወጥ እርሱን በመታዘዝ ለመኖር እንዲወስኑ የሚያደርግዎት ለምን ይመስልዎታል?**

*እርብ ታህሣሥ 7* *Dec 16*

## *ተጨማሪ ሀሳብ*

አሁን የዚህ ዓለም ፍርድ ደርሶአል፤" በማለት ክርስቶስ ቀጠለ፤ "አሁን የዚህ ዓለም ገዥ ወደ ውጭ ይጣላል፤ እኔም ከምድር ከፍ ከፍ ያልሁ እንደ ሆነ ሁሉን ወደ እኔ እስባለሁ፡፡" ይህንን ያለው እርሱ የሚሞተውን ሞት በማመልከት ነው፤ የዚህ ምድር ቀውስ ይህ ነው፤ የሰዎች ኃጢዓት መክፈያ ከሆንኩኝ፣ ይህች ምድር ብሩህ ትሆናለች፡፡ በሰዎች ህይወት ላይ ሰይጣን የዘረጋው ወጥመድ/አሽከላ ይሰበራል፡፡ የተበላሸው የእግዚብሔር ምስል በሰው ዘር ዘንድ ይታደሳል እናም የአማኝ ቅዱሳን ቤተሰብ በስተመጨረሻ ሰማያዊውን ቤት ይወርሳሉ፡፡ ይህ ነው የክርስቶስ ሞት ውጤት፡፡ መድሃኒዓለም ከፊት ለፊቱ የሚታየውን የአሸናፊነት ትዕይንት ከሚያስፈራው ባለ ግርማ ትዕይንት ጋር በማሰላሰል ተጠመደ፡፡

‹‹ነገር ግን የሰው ዘር የድነት ስራ በመስቀሉ ላይ የተሰራው ብቻ አይደለም፡፡ የእግዚአብሔር ፍቅር ለዩኒቨርስ ሁሉ ተገለጠ፡፡ የዚህ ዓለም ገዢ ተጣለ፡፡ ሰይጣን በእግዚአብሔር ላይ ያነሳው ክስ ውድቅ ሆነ፡ ፡ በሰማይ ላይ የተዘረጋው አመጽ ለዘለዓለም ተወገደ፡፡ መላዕክት እንዲሁም ሰዎች ሁሉ ወደ አዳኙ ተሳቡ፡ ፡›› ኤለን ጂ ኋይት፣ ዘ ዲዛየር ኦፍ ኤጅስ፣ ገጽ 625፣ 626 /በእንግሊዝኛው/

## የመወያያ ጥያቄዎች:

1. የኢየሱስ ህይወት እና ሞት የኢዮብ መጽሐፍ ሳይመልስ የቀራቸውን ጥያቄዎች የሚመልስልን ሌሎች መንገዶች ምን ምን ናቸው ብለው ያስባሉ?

2. የኢየሱስ መስቀሉ ስለ እግዚአብሔር ባህርይ፣ በተለይም የፈጠረን እርሱ በመስቀል ላይ የሞተልንም እርሱ ስለመሆኑ እስቲ ያሰላስሉ። ይህ ዕውነታ ምንም ዓይነት ፈተናዎች ቢገጥመን ለምንድነው የበዛ ተስፋ እና ምቾት የሚሆነን? ይህ አስደናቂ የሆነ ዕውነት እንዴት ነው በእግዚአብሔ እና በመልካምነቱ ላይ እንድንደገፍ የሚያደርገን? (ሮሜ. 8፡ 32)

3. እንደተመለከትነው፣ የኢዮብ መጽሐፍ፣ ሌሎች ነገሮችንም ጨምሮ፣ ታላቁ ተጋድሎ እጅግ ታላቅ ጉዳይ መሆኑን እንዲሁም በክርስቶስ እና በሰይጣን መካከል ያለ እና ከምድርም ይልቅ የሰፋ ነገር ስለመሆኑ አሳይቶናል። ኢየሱን በሰማያዊ ክብሩ ብቻ ያዩት እነዚያ የሰማይ ፍጥረታት፣ አሁን ደግሞ በመስቀል ላይ ባደረገው ነገር ውስጥ ሲያልፍ ሲያዩት ምን እንደተሰማቸው ለማሰብ ይሞክሩ። በዚህ አስደናቂ ሃሳብ ውስጥ ማሰላሰል በኢየሱስ አማካይነት ስለተሰጠን ነገር እንድናመሰግን የሚረዳን እንዴት ነው?